# ምዕራፍ አንድ

## 1. የነገረ ማርያም አስተምህሮ [Mariology] የት መጣና ዕድገት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ በሰፊው ተመዝግቦ እንደምንመለከተው ከአንደኛው እስከ አምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ የነበረችው ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን ዘምህሮ ቅዱሳን ወሠራዒ ሕግ ከሆነው ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ፣ የመጀመሪያዎቹ የወንጌል መምህራን ከሆኑት ከቅዱሳን ሐዋርያት ያልሰማችውና ያልተማረችው የእንግዳ ትምህርት ማዕበልና የኑፋቄ ሞገድ በእጅጉ ይፈታተናት ነበር:: በመሆኑም አብዛኞቹ የኑፋቄና የክሕደት ትምህርቶች [Heretical Teachings] የምሥጢረ ሥጋዌንና የነገረ ድኅነት አስተምህሮዋን የሚቃረኑ ናቸው::

የነገረ ማርያም ትምህርት ለምሥጢረ ሥጋዌ ትምህርት መሠረት በመሆኑ በወቅቱ የተነሡት ሊቃውንት አበው ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያናችን ስለ ነገረ ሥጋዌና ስለ ነገረ ድኅነት የምታምነውንና የምታስተምረውን አማናዊና ርቱዕ አስተምህሮ በስፋትና በጥልቀት ለማብራራትና ለመጠበቅ ብሎም በዘመኑ የነበሩትን የክሕደት ትምህርቶችንና አስተማሪዎችንም ለማረቅና ለማስተካከል ያደረጉት ከፍተኛ ጥረት ለነገረ ማርያም ትምህርት ዕድገትና መስፋፋት በር ከፋች ሆኗል::(5)

(5) አባ ጎርጎርዮስ፤ *የቤተክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ፤* (አዲስ አበባ፤ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፤ 1978 ዓ.ም.)፣ ገጽ 93-104፤ ተሾመ ዘሪሁን (መልአከ ታቦር) ፤ *ሰአሊ ለነ ቅድስት*፤ (አዲስ አበባ፤ ቅዱስ ጊዮርጊስ ማተሚያ ቤት፤ 1978 ዓ.ም.)፣ ገጽ 33-35:: Paul F. Palmer, *Mary in the Documents of the Church* (London: Burns Oates Ltd., 1953), 3-4. Tadros Y. Malaty (Fr.), *St. Mary in the Orthodox Concept*,

ይህ ደግሞ ወደፊት እንደምንመለከተው እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም "ወላዲተ አምላክ" [*Theotokos* - Mother of God] መሆኗን በመግለጥ እግዚአብሔር ወልድ በተዋሕዶ ሰው የሆነበትን የሥጋዌ ምሥጢር አማናዊነት [The Reality of the Incarnation] በግልጽ ያስተምሩ ነበር:: ከዚህም ጋር እመቤታችን "ወትረ ድንግል ማርያም፤ ዘለዓለማዊት ድንግል ማርያም" [Perpetual Virgin Mary] መሆኗን በማስረዳትና በማረጋገጥ የኢየሱስ ክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት [The Divinity of Jesus Christ] በአጽንኦት ይመሰክሩ ነበር::

በቅዱሳት መጻሕፍትና በታሪክ መዛግብት በስፋት እንደተገለጸው ሕዝቧ ሕዝበ እግዚአብሔር፣ ሀገሯም ሀገረ እግዚአብሔር የሆነችው ኢትዮጵያ ቅድመ ክርስትናም ሆነ ክርስትናን ከተቀበለች በኋላ ከአምልኮተ እግዚአብሔር የተለየችበትና የራቀችበት ጊዜ ባለመኖሩ ከፈጣሪዋ ጋር ያላት መንፈሳዊ ትሥሥር አያሌ ምዕተ ዓመታትን ያስቆጠረ ነው:: በዚህም ረጅምና ሥር የሰደደ ሃይማኖታዊ ጉዞዋ ምክንያት የጁዲዮ ክርስቲያን አገር [Judeo-Christian Country] በመባል ትታወቃለች::(6) ይህም ማለት ቅድመ ክርስትና መፍቀሬ ሰብእ የሆነው

---

Book IV (Alexandria: St. George Coptic Church, 1978), 32-39. Hilda Graef, *Mary: A History of Doctrine and Devotion* vol. 1 (London: Sheed and Ward Ltd., 1963), 51-52. Pelikan Jaroslav, *Mary Through the Centuries: Her Place in the History of Culture* (New Haven and London: Yale University Press, 1996), 48-51. B. Juniper Carol, *Mariology* vol. 2 (Milwaukee, New York: The Bruce Publishing Company, 1955), 120,

(6) ቅዱስ ሲኖዶስ፤ *የዛሬዋ ኢትዮጵያ የቅዱሳት መጻሕፍት፣ የታሪክና የሥነ ጥንት ኢትዮጵያ ናት፤* (አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፤ 1982 ዓ.ም)፤ ገጽ 41-63:: በአገራችን ታሪክ እንደተመዘገበው ንግሥተ ሳባ በቅድስት አገር በኢየሩሳሌም ባደረገችው ቆይታዋ ጊዜ ከንጉሥ እስራኤል ከሰሎሞን ቀዳማዊ ምኒልክን እንደፀነሰች፤ ልጁ ተወልዶ ካደገ በኋላም የአባቱን አገር ለማየት ወደ ኢየሩሳሌም እንደሄደ፤ ከጉብኝቱም ሲመለስ ታቦተ ጽዮንን፣ ሌዋውያን ካህናትንና የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ወደ ኢትዮጵያ ይዞ እንደመጣ እንመለከታለን:: ሉሌ መልአኩ፤ *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፤* (አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፤ 1997 ዓ.ም.)፣ ገጽ 13-17:: Sergew Hable Selassie, "The Establishment of the Ethiopian Church," Sergew Hable Selassie et. al. *The Church of Ethiopia: A Panorama of History and Spiritual Life* (Addis Ababa: Berhanena Selam Printing Press, 1997), 1-3. አባ ጎርጎርዮስ፤ *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፤*



ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር በዘመነ ብሉይ በነበሩ በቅዱሳን አበውና በቅዱሳን ነቢያት አማካይነት የገለጠውንና ለቤተ እስራኤል የሰጠውን ሥርዓተ አምልኮ ወይም የአይሁድን እምነት [Judaism] የተቀበለች አገር ናት::

ለዚህም ቅድመ ልደተ ክርስቶስ የነበረችው የሳባ ንግሥት ወደ ቅድስት አገር ወደ ኢየሩሳሌም ያደረገችው ታላቅ ሃይማኖታዊ ጉዞ ጉልህ ማስረጃ ነው:: (1ኛ ነገሥ. 10÷1-13፤ ማቴ. 12÷42፤ ሶፎ. 3÷10) ይህንንም አስመልክቶ ልበ አምላክ የተባለው ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊት ሲናገር "ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር፤ ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች" (መዝ. 67÷31) በማለት በአጽንኦተ ቃል መስክሮአል:: በዚህም ቃለ ትንቢት መሠረት ኢትዮጵያችን እደ ኀሊናቸውንና እደ ልቡናቸውን ዘወትር በአምልኮተ እግዚአብሔር፣ በጾምና በጸሎት፣ በምጽዋትና በትሩፋት ዘርግተው፣ በሃይማኖት ጸንተው፣ በምግባር ቀንተው የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የሚኖሩባት በመሆኗ አገሪቱ ሀገረ እግዚአብሔር፣ ሕዝቧም ሕዝበ እግዚአብሔር መሆኑን ልብ ይሏል::

በአገራችን ረጅም ሃይማኖታዊ ሕይወት ውስጥ ሰፊ ቦታ የሚሰጠው ይህ ታሪካዊ ጉዞ በቀዳማዊ ምኒልክ አማካይነት ለታቦተ ጽዮን፣ ለሌዋውያን ካህናትና የተለያዩ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ወደ አገራችን መግባት በር ከፋች ሆኗል::(7) ስለሆነም በወቅቱ በኢትዮጵያ

---

(አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፤ 1993 ዓ.ም.)፣ ገጽ 15-19:: ቅዱስ ሲኖዶስ፤ *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት፣ ሥርዓተ አምልኮና የውጭ ግንኙነት፤* (አዲስ አበባ፤ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፤ 1989 ዓ.ም.)፣ ገጽ 5-7:: Abba Melketsedek, *The Teaching of the Ethiopian Orthodox Church* (Danville, CA: Alem Publishers, 1997), 88-92.

(7) ሉሌ መልአኩ (መምህር)፣ *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፤* ገጽ 21-22:: አባ ጎርጎርዮስ፤ *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፤* ገጽ 20-21:: ቅዱስ ሲኖዶስ፤ *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት፣ ሥርዓተ አምልኮና የውጭ ግንኙነት፤* ገጽ 100-108. Andualem Dagmawi, *A Glance into History of the Ethiopian Orthodox Tewahedo Church* (Toronto:

የነበረው የኦሪት እምነትና ሥርዓት እንዲስፋፋና እንዲጠናከር ከፍተኛ አስተዋጽኦ በማድረጉ ይህ ዘመን ለአገራችን አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ነው።

ይህ በዚህ እንዳለ ሀገረ እግዚአብሔር የሆነችው ኢትዮጵያችን የክርስትና ሃይማኖት ከተመሠረተባትና ከመነጨባት ከምድረ እስራኤል (ኢየሩሳሌም) ቀጥላ ክርስትናን የተቀበለችው በአንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን በዘመነ ሐዋርያት ነው። ይህም ሊሆን የቻለው በ34 ዓ. ም. በኢትዮጵያዊው ጃንደረባ በመልከ ጸዴቅ ወይም ባኮስ አማካይነት የክርስትና ሃይማኖት ወደ ምድረ ኢትዮጵያ በመምጣቱ ነው።[8] በመጽሐፈ አብርክሲስ (ግብረ ሐዋርያት) እንደተጻፈው ቅድመ ክርስትና በአገራችን በነበረው እምነት መሠረት ሥርዓተ አምልኮን ለመፈጸም ወደ ቅድስት አገር ወደ ኢየሩሳሌም ሊሰግድ የሔደው የንግሥት ህንደኬ ጃንደረባ ከዐበይት ነቢያት መካከል አንዱ የሆነው ልዑለ ቃል ኢሳይያስ ስለ መሲሕ ክርስቶስ ሰው መሆንና ወደዚህ ዓለም መምጣት እንዲሁም ሊፈጽመው ስላለው የቤዛነት ሥራ የተናገረውን ዐቢይ ቃለ ትንቢት በሠረገላው ላይ ተቀምጦ ያነብ ነበር።

ይሁን እንጂ ጃንደረባው የገጸ ንባቡን ትርጓሜ ምሥጢር ስላልተረዳ መጽሐፍ "ሁሉ መዳንን ይወርሱ ዘንድ ስላላቸው ለማገዝ የሚላኩ የሚያገለግሉም መላእክት አይደሉምን?" (ዕብ. 1÷14) እንዳለ በመልአከ እግዚአብሔር ትእዛዝ ሐዋርያው ቅዱስ ፊልጶስ ወደ ሰረገላው ቀርቦ የትንቢቱን ፍጻሜ አብራርቶ መሰከረለት። በዚህም ምክንያት ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ በሐዋርያው ስብከት ላይ ተመሥርቶ የኢየሱስ ክርስቶስን ሰው የመሆን ምሥጢር አምኖ ተቀበለ። ታላቁ ሐዋርያ ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ "ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃልና፣

St. Mary's Cathedral, 2005), 2. Sergew Hable Selassie, "The Establishment of the Ethiopian Church," 3.

(8) አባ ጎርጎርዮስ፣ *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ*፣ ገጽ 20-21። *መሠረት ስብሐት ለአብ*፣ *ስምዓ ጽድቅ ብሔራዊ*፣ (አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1951 ዓ.ም.)፣ ገጽ 28-31።



በአፉም መስክሮ ይድናል" (ሮሜ 10÷10) በማለት እንደተናገረው ጃንደረባው ይህንን ቀጥተኛ እምነቱንም በቅዱስ ፊልጶስ ፊት "ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አምናለሁ" ሲል ገልጦ መሰከረ። በመጨረሻም ይህ ጃንደረባ መድኅነ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር ሕያው፤ ወልደ ማርያም ሥጋው መሆኑን በምታምንና በምታሳምን "ወልድ ዋሕድ" ሃይማኖት አምኖ በእደ ፊልጶስ በፈቃዱ ተጠመቀ። (የሐዋ. ሥራ 8÷26-39)

ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ በዘመነ ሐዋርያት የክርስትናን እምነት መቀበሉን አስመልክቶ የእስክንድርያው ሊቅ አርጌንስ "እናንተ የኢየሩሳሌም ቆነጃጅት ሆይ፣ እኔ ጥቁር ነኝ፤ ነገር ግን ውብ ነኝ።" (መኃ. ዘሰሎ. 1÷5) የሚለውን የመኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን ገጸ-ንባብ በተረጐመበት ድርሳኑ ሲናገር:- "ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች" (መዝ. 67÷31) የሚለው የነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊት ቃለ ትንቢት ፍጻሜ መሆኑን መስክሮአል።[9]

"የቤተ ክርስቲያን ታሪክ አባት" በመባል የሚታወቀው ታላቁ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊ አውሳብዮስም ስለ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ በተናገረበት አንቀጽ "በመላው ዓለም የመጀመሪያው የክርስትና እምነት (የአማኞች) ፍሬ ሆነ" ["The first-fruits of believers throughout the world"] ብሎ ተናግሮለታል። ከዚህም ጋር ሕጽው ወደ አገሩ ምድር ከተመለሰ በኋላ "ለወገኖቹ ሐዋርያና ሰባኪ ሆነ"[10] ብሏል።

ከላይ እንደገለጥነው ምንም እንኳን ኢትዮጵያችን ከክርስትና እምነት ጋር የተዋወቀችው በአንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን ቢሆንም

(9) Origen, "The Song of Songs: Commentary and Homilies," trans. R. P. Lawson and eds. Johannes Quasten and Joseph C. Plumpe *Ancient Christian Writers: The Works of the Fathers in Translation, No. 26* (Westminster, Maryland: The Newman Press, 1957), 102-103.

(10) Eusebius, *The History of the Church from Christ to Constantine,* trans., G. A. Williamson (Minneapolis, Minnesota: Augsburg Publishing House, 1975), 74. Archbishop

ክርስትና የአገራችን ብሔራዊ ሃይማኖት መሆኑ በይፋ የታወጀው በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነው:: ስለሆነም ይህ ጊዜ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሁለንተናዊ ሕይወት ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል:: ከእነዚህም መካከል አንደኛው በ330 ዓ.ም. በነገሥታት አብርሃ ወአጽብሐ (ኢዛናና ሳይዛና) ዘመነ መንግሥት ክርስትና ብሔራዊ ሃይማኖት መሆኑ እምነቱ በመላው አገሪቱ እንዲስፋፋና እንዲጠናከር መንገድ ጠራጊ ሆኗል:: ሁለተኛው ደግሞ ሃያ አምስተኛው የእስክንድርያ ፓትርያርክ የነበረው ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ ቅዱስ ፍሬምናጦስን (አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን) የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ጳጳስ አድርጎ ሾሞ የላከልን በዚሁ ክፍለ ዘመን ነው:: ይህም ቤተ ክርስቲያናችን በሐዋርያት ኤጲስ ቆጶሳዊ የአስተዳደር መንበር እንድትቋቋምና እንድትጠናከር አድርጓታል::

ከዚያን ጊዜ ጀምሮም ከሣቴ ብርሃን አባ ሰላማ አያሌ ካህናትንና ዲያቆናትን በመላ አገሪቱ እየተዘዋወረ በመሾሙ ለክርስትና ሃይማኖት መሠረት የሆኑት ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን በአግባቡ ለመፈጸም አስችሎአል:: ሦስተኛው ደግሞ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ ጋር የነበራት መንፈሳዊ ግንኙነትና ሃይማኖታዊ ትሥሥር የመጀመሪያው ዓለም አቀፍ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ በሆነው በጉባኤ ኒቅያ የተወሰነውና የተረቀቀው ኦርቶዶክሳዊ እምነት እንዲስፋፋና እንዲያብብ ምቹ ሁኔታዎችን ፈጥሮአል:: በዚህም መሠረት በአብዛኞቹ የታሪክ ምሁራንና የሥነ መለኮት ሊቃውንት ዘንድ [Historical and Theological Scholars] የኢትዮጵያ ክርስትና ሃይማኖት ቅድመ ኬልቄዶን የነበረው ኦርቶዶክሳዊ እምነት ["Pre-Chalcedonian Orthodoxy"]

Yeshaq, *The Structure and Practice of the Ethiopian Church Liturgy* (Bermuda, No Publisher, 1983), 3. Christian Frederick Cruse and Isaac Boyle trans., *The Ecclesiastical History of Eusebius Pamphilus,* Popular Edition (Grand Rapids, Michigan: Baker Book House, 1979), 50. Ethiopian Orthodox Church Patriarchate, *The Church of Ethiopia Past and Present* (Addis Ababa: Commercial Printing Enterprise, 1997), 9-11. አባ ጎርጎርዮስ፤ *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ*፤ ገጽ 21::



መሆኑ በግልጽ የታወቀና የተረጋገጠ እውነታ ነው::(11)

ከዚህ በተጨማሪ በ480 ዓ.ም. የተሰዓቱ (የዘጠኙ) ቅዱሳን አበው ከሶርያና ከታናሽ እስያ እንዲሁም ከቢዛንታይን ግዛቶች ወደ ኢትዮጵያ መምጣት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሁለንተናዊ ሕይወት ዕድገት ውስጥ ቀጣዩ ዐቢይ የታሪክ ምዕራፍ ነው:: እኒህ ቅዱሳን አበው በወቅቱ ተከስቶ የነበረውን የኬልቄዶናውያንን የሁለት ባሕርይ እንግዳ ትምህርት አንቀበልም በማለታቸውና ከቀደሙት ቅዱሳን አበው በአደራ የተቀበሉትንና ወልድ ዋሕድ የምትለውን ኦርቶዶክሳዊ እምነታቸውን አጽንተው በመያዛቸው ምክንያት በዘመኑ በነበረው የቢዛንታይን መንግሥት በግፍ ተሰድደው ወደ አገራችን የመጡ ኦርቶዶክሳውያን አበው ናቸው::

ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችንም የእነዚህን ቅዱሳን አበው ሐዋርያዊ አገልግሎትና መንፈሳዊ ተጋድሎ በመመልከት መጽሐፍ «ወአለሰ ይጠይቁ ብዙኃነ ሰብአ ኀበ ጽድቅ ወያበርሁ ከመ ከዋክብተ ሰማይ ለዓለመ ዓለም፤ ብዙዎችንም ወደ ጽድቅ የሚመልሱ እንደ ከዋክብት ለዘላለም ይደምቃሉ» (ዳን. 12÷3) እንዳለ በስማቸው ጽላት ቀርጻ፣ የመታሰቢያ ቤተ ክርስቲያን አንጻ ውለታቸውን ስትዘክር

(11)Archbishop Yeshaq, "The Ethiopian Orthodox Church," Robert F. Taft ed. *The Oriental Orthodox Churches in the United States* (Washington D.C.: United States Catholic Conference, Inc., 1986), 12. ኪዳነ ወልድ ክፍሌ (አለቃ)፣ *መጽሐፈ ሰዋስው ወግሥ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ*፣ (አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1948 ዓ.ም.)፣ ገጽ 383-384:: Samuel A. B. Mercer, *The Ethiopic Liturgy : Its Sources, Development, and Present Form* (Milwaukee: The Youngmen Church Company, 1925), 83-85. ቅዱስ ሲኖዶስ፣ *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት፣ ሥርዓተ አምልኮና የውጭ ግንኙነት*፣ ገጽ 6-7:: ሉሌ መልአኩ (መምህር)፣ *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ*፣ ገጽ 24-25:: አባ ጎርጎርዮስ፣ *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ*፣ ገጽ 21-25:: Aymro Wondemagegnehu and Joachim Motovu eds., *The Ethiopian Orthodox Church* (Addis Ababa: The Ethiopian Orthodox Mission, 1970), 4. Abba Melketsedek, *The Teaching of the Ethiopian Orthodox Church,* 93-96. Marylin E. Heldman, *The Marian Icons of the Painter Fre Seyon: A Study in Fifteenth Century Ethiopian Art, Patronage, and Spirituality* (Wiesbaden: Orientalia Biblica et Chirstiana, 1994), 12.

ትኖራለች:: ተሰዓቱ ቅዱሳን ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዘርፈ ብዙ አስተዋጽኦዎች አበርክተዋል:: ከእነዚህም መካከል ስብከተ ወንጌልን ማስፋፋትና ለሁሉ እንዲዳረስ ማድረግ፣ የተለያዩ ገዳማትን በመመሥረት ገዳማዊ ሕይወት በአገራችን እንዲያብብና እንዲጠናከር ማድረግና አያሌ ቅዱሳት መጻሕፍትን እንዲሁም በርካታ የጸሎትና የሥርዓተ አምልኮ መጻሕፍትን ከጥንታውያን ቋንቋዎች ማለትም ከጽርዕ (ከግሪክ)፣ ከዕብራይስጥና ከሶርያ ወደ ግዕዝ ቋንቋ መመለስ (መተርጎም) ይገኙባቸዋል::[12]

ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን በዘወትር ሥርዓተ አምልኮዋ ጊዜ የምትገለገልባቸው የተለያዩ የጸሎትና የቅዳሴያት መጻሕፍቶች ሁሉ የነገረ ማርያም አስተምህሮዋን በስፋትና በጥልቀት የሚያስረዱና የሚመሰክሩም ናቸው:: ይልቁንም ደግሞ ወደፊት በስፋት እንደምናየው ፍጹም ሰማያዊና መንፈሳዊ የሆነው የቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓተ ቅዳሴ በማኅፀነ ድንግል ማርያም የተጀመረውን፣ በድንግልናዊ ልደት የተገለጠውን፣ በቀራንዮ አደባባይ የተፈጸመውንና በዕለተ ትንሣኤ የተረጋገጠውን የድኅነተ ዓለም ጉዞ (አምላካዊ መግቦት) ዘወትር የሚያዘክርና የሚያወሳ የነገረ ማርያምና የነገረ ድኅነት የምሥጢር መድበል ነው:: በዚህም "የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ሁለንተናዊ ሕይወት ከእግዚአብሔር የማዳን ሥራ ጋር በእጅጉ የተዋሐደና በቀጥታ የተገናኘ" መሆኑን ይመሰከቷል::[13] ይልቁንም ይህ ጥልቅና ድንቅ ምሥጢር ስፍሐ አእምሮ ያላቸውና የነገረ መለኮትን ትምህርት በቅጥነተ ኅሊና የመመርመርና የማራቀቅ ተውህቦና ክሂሎት የተሰጣቸው ኦርቶ

[12] Ethiopian Orthodox Church Patriarchate, *The Church of Ethiopia Past and Present*, 12-13. አባ ጎርጎርዮስ፣ *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ*፣ ገጽ 25-26:: ቅዱስ ሲኖዶስ፣ *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት፣ ሥርዓተ አምልኮና የውጭ ግንኙነት*፣ ገጽ 122-123:: Aymro Wondemagegnehu and Joachim Motovu eds., *The Ethiopian Orthodox Church*, 4. ሉሌ መልአኩ (መምህር)፣ *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ*፣ ገጽ 28-29::

[13] Archbishop Yeshaq, *The Structure and Practice of the Ethiopian Church Liturgy*, i. አባ ጎርጎርዮስ፣ *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ*፣ ገጽ 131-132::



ዶክሳውያን ሊቃውንት ባስተማሩት ሕያው ትምህርትና በጻፏቸው አያሌ መጻሕፍት ከርሠ ምሥጢር ውስጥ እንደ ዕንቁ ፈርጥ ሲያበራ ይታያል::

የተሰዓቱ ቅዱሳን ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ቤተ ክርስቲያናችንን የሶርያ ቤተ ክርስቲያን ከምትጠቀምባቸውና ልዩ ልዩ ሊቃውንት ከደረሷቸው የጸሎትና የአምልኮ መጻሕፍት ጋር እንድትተዋወቅ አድርጓታል:: ከዚህም ጋር በሁለቱ እኅት አብያተ ክርስቲያናት መካከል የጠበቀ ግንኙነት እንዲፈጠር ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል:: በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ካህናትና ምእመናን ዘንድ በሰፊው ከሚታወቁትና በቤተ ክርስቲያናችን የዘወትር አገልግሎት ውስጥ ከፍተኛ ቦታ ካላቸው መጻሕፍተ ውዳሴያት አንዱና ዋነኛው "ውዳሴ ማርያም" የተሰኘው የሶርያዊው ሊቅ የቅዱስ ኤፍሬም[14] የምስጋና ድርሰት ነው:: ይህ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ውዳሴ በየዕለቱ የኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች የጸሎት ሕይወት

[14] ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረ የምሥራቅ ቤተ ክርስቲያን አባት ነው:: በዜና አበው ሊቃውንት [Patristic Scholars] ዘንድ "የመንፈስ ቅዱስ በገና፣ ዕንዚራ"፤ እንዲሁም "የመንፈስ ቅዱስ ዋሽንት፣ ቅኝት" በመባል ይታወቃል:: ከጣዕመ ድርሰቱም የተነሣ አያሌ የቤተ ክርስቲያን የሥነ ጽሑፍ ምሁራን "ከሶርያውያን ገጣሚዎችና ደራሲዎች ሁሉ የላቀና የመጠቀ ችሎታና ተውህቦ ያለው" አባት እንደሆነ ይመሰክሩለታል:: Sebastian Brock, trans., *The Bride of Light: Hymn on Mary from the Syriac Churches* (Kottayam, Kerala: St. Joseph's Press, 1994), 13. Eric L. Mascall, "The Mother of God," *Mary's Place in Christian Dialogue* (Wilton, Connecticut: Morehouse-Barlow Co., Inc., 1983), 53, 182. ቅዱስ ኤፍሬም በጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ከሚታወቅባቸው ሥራዎቹ አንዱና ዋነኛው የሆነው "የውዳሴ ማርያም" ድርሰቱ ነው:: ይህ ታላቅ ሊቅ በዚህ የእመቤታችን ጣዕመ ውዳሴው ስለ ቅድስት ድንግል እመቤታችን ወላዲተ አምላክነት፣ ስለ ዘለዓለማዊ ድንግልናዋ፣ ስለ አማላጅነቷ፣ ስለ ንጽሕናዋና ቅድስናዋ አምልቶና አስፍቶ ተናግሮላታል:: ይልቁንም አምላክ የሰው ልጆችን ለማዳን ባደረገው አምላካዊ የቸርነት ሥራው ውስጥ ያላትን ታላቅና ሰፊ ድርሻ አጉልቶ አሳይቶአል:: በዚህም ምክንያት ይህ የቅዱስ ኤፍሬም የእመቤታችን ምስጋና ለጥንታውያን የኦሪየንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት (ግብጽ፣ ሶርያ፣ አርመን፣ ሕንድና ኢትዮጵያ) የነገረ ማርያም ትምህርት ዕድገትና መስፋፋት ከፍቱኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል:: John Panicker (Fr.), *Notes on Patrology* (Addis Ababa: Holy Trinity Theological College, 1996), 52. G. G. Meersseman trans. *The Acathistos Hymn: Hymn of Praise to the Mother of God* (Fribourg, Switzerland: The University Press, 1958), 11.

ውስጥ ልዩ ሥፍራ አለው::

ይህ የውዳሴ መጽሐፍ በሳምንት ውስጥ በሚገኙት ሰባት ቀናት መሠረት በሰባት ዋና ዋና ክፍሎች የተከፈለ[15] ሲሆን በውዳሴው ውስጥ የሚገኘው እያንዳንዱ ገጸ ንባብ ነገረ ሥጋዌንና ምሥጢረ ድኅነተ ዓለምን አስመልክቶ በዘመነ ብሉይ በተገለጠው ኅብረ አምሳል የታጀበ፣ በዐበይት ነቢያትና በደቂቀ ነቢያት በተነገሩ የተለያዩ ኅብረ ትንቢቶች የዳበረና የበለጸገ የነገረ ድኅነት የምሥጢር መድበል ነው:: ከዚህም ጋር ይህ ቃለ ውዳሴ በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በስፋት የተመዘገቡትን የእነዚህን ኅብረ አምሳልና ኅብረ ትንቢት ፍጻሜ በዘመነ ሐዲስ ከተከናወነው የድኅነተ ዓለም ሥራ ጋር በማገናዘብ ወላዲተ አምላክ በነገረ ድኅነት ውስጥ ያላትን መሠረታዊና መጠነ ሰፊ ድርሻ በመጽሔተ አሚን ቁልጭ አድርጎ ያሳያል::

ከላይ እንደተመለከትነው በየዘመናቱ የተነሡት አያሌ ኦርቶዶክሳውያን የሥነ መለኮት ሊቃውንት ምሥጢረ ሥጋዌን አስመልክቶ በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በስፋት የተገለጡትን አያሌ ኅብረ አምሳልና ኅብረ ትንቢት በየትምህርቶቻቸው አመሥጥረውና አራቅቀው ማስተማራቸው፤ እንዲሁም በየድርሳኖቻቸው ውስጥ በንጽጽር አብራርተውና አስፋፍተው መጻፋቸው ለምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት የነገረ ማርያም ትምህርት [Mariological Teaching] ጠንካራ መሠረት ጥሏል::[16]

[15] *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣* (አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ 1983 ዓ.ም.)፣ ገጽ 14-17:: Messale Engeda (Liqa Kahinat), *Handbook of Ethiopia Orthodox Church* (Toronto: ABC Publishing, 1986), 24.

[16] Getachew Haile (Professor), *The Mariology of Emperor Zara Yaqob of Ethiopia* vol. 24 (Rome: Orientalia Christiana Analecta, 1992) 1. Heldman, *The Marian Icons of the Painter Fre Seyon: A Study in Fifteenth Century Ethiopian Art, Patronage, and Spirituality,* 178. Messale Engeda (Liqa Kahinat), *Handbook of Ethiopian Orthodox Church,* 24. ቅዱስ ሲኖዶስ፣ *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት፣ ሥርዓተ አምልኮና የውጭ ግንኙነት፣* ገጽ 44-46::



እንደሚታወቀው በስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ማለትም ከተሰዓቱ ቅዱሳን ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ጥቂት አሥርተ ዓመታት በኋላ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ወደ አዲስ የወርቃማ ዘመን ተሸጋግራለች:: ይህም ሊሆን የቻለው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የዜማ መሠረት የሆነው ታላቁ ሊቅ ቅዱስ ያሬድ የተነሣበት ወቅት በመሆኑ ነው:: ይህ ኢትዮጵያዊ የዜማ ደራሲና ሊቅ ቤተ ክርስቲያናችን ከዓመት እስከ ዓመት ድረስ የምትገለገልባቸውን ልዩ ልዩ የዜማ ስልቶች ከወቅቱ ጋር እያስማማ የደረሰና የቀመረ የዜማና የቅዱሳት መጻሕፍትም ሊቅ ነው::[17]

በመሆኑም የቅዱስ ያሬድ የዜማ ድርሰቶች (ድጓ፣ ጾመ ድጓ፣ ዝማሬ፣ መዋሥዕትና ምዕራፍ) በቅዱሳት መጻሕፍት ምሥጢር የተቀመሙና የበለጸጉ ናቸው:: በዚህም ምክንያት ስለ እመቤታችን ወላዲተ አምላክነት፣ ዘለዓለማዊ ድንግልና፣ ስለ ንጽሕናዋ፣ ስለ ቅድስናዋና ስለ ክብሯ እንዲሁም በነገረ ድኅነት ውስጥ ስላላት ከፍተኛ ድርሻ አምልተውና አስፍተው የሚናገሩና የሚመሰክሩ በመሆናቸው ስለ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የነገረ ማርያም አስተምህሮ በቂና የዳበረ ግንዛቤ ያስጨብጣሉ::

ከላይ በዝርዝር በተገለጸው መሠረት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የነገረ ማርያም አስተምህሮ የትመጣ (መነሻው) ከአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ መሆኑን ልብ ይሏል:: በቤተ ክርስቲያን ታሪክ በስፋት ተመዝግቦ እንደምናየው ይህ ዘመን

[17] ቅዱስ ሲኖዶስ፣ *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት፣ ሥርዓተ አምልኮና የውጭ ግንኙነት፣* ገጽ 7፣ 45-46:: Archbishop Yeshaq, *The Structure and Practice of the Ethiopian Church Liturgy,* 5-10. ሉሌ መልአኩ (መምህር)፣ *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፣* ገጽ 40-45:: Getachew Haile (Professor), *The Mariology of Emperor Zara Yaqob of Ethiopia,* 1. See also W. Wright, *Catalogue of the Ethiopic Manuscripts in the British Museum Acquired Since the Year 1847* (London: Gilbert and Rivington, 1887), 144-117. Paul Verghese, "Ethiopian Worship," *A Dictionary of Liturgy and Worship,* ed. J. G. Davies (New York: McMillan, 1972), 172.

አርዮሳዊ ክሕደት ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያንን በእጅጉ የሚፈታተንበት ከባድ ጊዜም ነበር:: በመሠረቱ ይህ አርዮሳዊ የክሕደትና የኑፋቄ ትምህርት በቅድሚያ የሚቃወመው የክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት ሲሆን በአንጻሩ ግን ትምህርቱ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ መሆኗንም ጭምር የሚቃረንና የሚያሳብል ትምህርት ነው:: በሌላ አገላለጽ ስንመለከተው ደግሞ እንደ አርዮስ አባባል ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክ ካልሆነ እሱን በሥጋ የወለደችው እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያምም እመ አምላክ፣ ወላዲተ አምላክ አይደለችም ማለት ነው::

ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንትም ነገረ ማርያም የነገረ ድኅነት መሠረት፣ የምሥጢረ ሥጋዌ መቅድም ነው የሚሉትም በዚህ ዐቢይ ምክንያት ነው:: ምንም እንኳን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የነገ ረ ማርያም አስተምህሮ በቅዱስ ኤፍሬምና በቅዱስ ያሬድ ድርሰቶች የበለጠ ቢዳብርና ቢስፋፋም ቅሉ የቤተ ክርስቲያናችን የነገረ ማርያም ትምህርት ከፍተኛ ደረጃ ላይ ሊደርስ የቻለው በአሥራ አምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በነበረው ታዋቂውና ታላቁ የኢትዮጵያ ንጉሥ በዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ[18] ዘመነ መንግሥት (1434-1468 ዓ.ም.) ነው:: ከምክንያቶቹም አንዱና ዋነኛው በወቅቱ ከነበረው የእስጢፋኖሳውያን የስሕተት ትምህርት ጋር የተደረገው ታላቅ ሃይማኖታዊ ክርክር ነው::[19]

[18] ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ በአሥራ አምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረ ታላቅ ኢትዮጵያዊ ንጉሥ ነው:: ለኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ እምነት ከነበረው ታላቅ መንፈሳዊ ቅናትና ከሚያሳየው ትጋት እንዲሁም በወቅቱ ከነበረው ጥልቅና ሰፊ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ክሂሎቱ የተነሣ "ኢትዮጵያዊው ካህንና ንጉሥ" በመባል ይታወቃል:: Taddesse Tamrat (Professor), "Some Notes on the Fifteenth Century Stephanite 'Heresy' in the Ethiopian Church," *Rassegna Di Studi Etiopici,*, V, XXII- Gennaio-Decembere: I. P. O. 1966), 103-104, 111. የዚህን ታላቅ ንጉሥ ኦርቶዶክሳዊ ሊቅነት አስመልክቶ ሄልድማን የተባለች የታሪክ ምሁር ስትናገር "ዘርዐ ያዕቆብ ሊቁ (ምሁሩ) ንጉሥ" ሊባል ይገባዋል በማለት መስክራለች:: Heldman, *The Marian Icons of the Painter Fre Seyon: A Study in Fifteenth Century Ethiopian Art, Patronage, and Spirituality,* 198-199.

[19] Getachew Haile (Professor), *The Mariology of Emperor Zara Yaqob of Ethiopia,* 1, 63-65. ጌታቸው ኃይሌ (ፕሮፌሰር)፣ *ደቂቀ እስጢፋኖስ በሕግ አምላክ*፣ (ሚኒሶታ፣



በታሪክ እንደምንረዳው በ1428 ዓ.ም. የተጀመረው ይህ የእስጢፋኖሳውያን እንቅስቃሴ በብዙዎች ክርስቲያኖች ዘንድ "ፀረ ማርያም" እና "ፀረ መስቀል" እንቅስቃሴ በመባል ይታወቅ ነበር:: ይልቁንም የእስጢፋኖሳውያን አባት የሆነው አባ እስጢፋኖስ ለዘመናት የቆየውን የቤተ ክርስቲያኒቱን ትውፊታዊ ውርስ እንዲሁም አገር በቀል የሆኑትን ሃይማኖታዊ ጣዕምና ለዛ ያላቸውን ባህሎችና ልምዶችን ይቃወምና ያጣጥል ስለነበር በዘመኑ የነበረችውን የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን አንድነትና ጽናት በእጅጉ ይፈታተን ነበር:: ይሁን እንጂ ኦርቶዶክሳዊው ንጉሥ ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ በወቅቱ ያደረገው ከፍተኛና ያላሰለሰ ጥረት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን ለማዳከምና ብሎም አንድነቷን ለመከፋፈል ምቹ ሁኔታን ይፈጥር የነበረውን ይህን ችግር ለመግታት ችሏል:: ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ በደቂቀ እስጢፋ(ኖስ) ምክንያት የተከሰተውን ይህንን ችግር ለማስወገድና ለመፍታት ካደረጋቸው ብርቱ ጥረቶች መካከል አንዱና ዋነኛው በ1450 ዓ.ም በደብረ ምጥማቅ ያደ ረገው ሃይማኖታዊ ጉባኤ እንደነበር ይነገርለታል::[20]

ኮሌጅቪል፤ ሊተርጂካል ፕሬስ፣ 2004) ገጽ 25-31:: በታሪክ ተጽፎ እንደምናገኘው እስጢፋኖሳውያን (ደቂቀ እስጢፋኖስ) የሚባሉት በአሥራ አምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበሩና አገር በቀል የሆኑ የክርስትና እምነት ተከታዮች ናቸው:: ይሁን እንጂ "እስጢፋኖሳውያን" በዘመኑ በነበረው ንጉሥ በዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ አማካኝነት በአገራችን ምእመናን ዘንድ በስፋት ይታወቅና ይሠራበት የነበረውንና "ለእመቤታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም፣ ለቅዱስ መስቀልና ለቅዱሳት ሥዕሳት ክብርና የጸጋ ስግደት ይገባል" የሚለውን ክርስቲያናዊና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት አንቀበልም በማለታቸው ከኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አንድነት ተለይተው ይኖሩ እንደነበር የተለያዩ የታሪክ መዛግብት ያስረዳሉ:: እኒህ ወገኖች "እስጢፋኖሳውያን"፣ "ደቂቀ እስጢፋኖስ፣ ደቂቀ እስጢፋ" ማለትም "የእስጢፋኖስ ልጆች፣ የእስጢፋኖስ ተከታዮች" በሚል ስያሜ ይጠሩ የነበረበት ዋነኛው ምክንያት መሪያቸውና አስተማሪያቸው አባ እስጢፋኖስ የተባለው አባት ስለነበር ነው:: ይህም አባት የአባ ሳሙኤል ዘደብረ ቈየጻ ገዳም ማኅበረ አበው ወአኃው መካከል እንደነበር ይነገርለታል:: *Gadla Abuna Abakerazun,* ed. & tran. Conti Rossini, *Corpus Scriptorum Christianorum Orientalium,* Vol. 56, *Scriptores Aethiopici,* t. 25 (text), 1954, 8-25, 113. ይሁን እንጂ በ1996 ዓ.ም. ታትሞ የወጣው "*ገድለ አቡነ እስጢፋኖስ ዘገንዳገንዶ*" የተሰኘው መጽሐፍ አባ እስጢፋኖስ የስሕተት ትምህርት የሌለባቸው ደገኛ አባት መሆናቸውን ይገልጻል::

[20] አባ ጎርጎርዮስ፣ *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ*፣ ገጽ 49፣ 101-102:: ደብረ ምጥማቅ በአገራችን ውስጥ በሰሜን ሸዋ ክፍለ ሀገር የምትገኝ

ሐዋርያዊት የሆነችው ቤተ ክርስቲያናችን ባሳለፈቻቸው ረጅምና ሰፊ የታሪክ ዘመናት ውስጥ እንደምንመለከተው ሕልውናዋን የሚፈታተን፣ አንድነቷን የሚከፋፍልና አማናዊ ትምህርቷን የሚያሳብል ፈተና ከውስጥም ሆነ ከውጭ ገጥሟታል:: ይሁን እንጂ የተለያዩ ጠላቶች በተነሡባት ጊዜ በአንጻሩ ደግሞ ፈተናውን ሁሉ በጽናት ተቋቁመው በአፍም በመጽሐፍም የእምነቷንና የሥርዓቷን ድንበር የሚያስከብሩ አያሌ ሊቃውንት መነሣታቸው የግድ ነበር:: በመሆኑም በዘመነ አርዮስ ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊን፣ በዘመነ ንስጥሮስ ደግሞ «የመናፍቃን መዶሻ» የተባለውን ቅዱስ ቄርሎስን ያስነሣ አምላክ በዘመነ እስጢፋኖሳውያን ደግሞ «ኢትዮጵያዊው ቄርሎስ» በመባል የሚታወቀውን አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ (ሳግላዊ) ለቤተ ክርስቲያን በማስነሣቱ «መጽሐፈ ምሥጢር» የተሰኘውንና ጥልቅና ረቂቅ የሆነውን የቤተ ክርስቲያናችንን የነገረ ማርያምና የምሥጢረ ሥጋዌ ትምህርት በሚገባ አምልቶና አስፍቶ የሚያስረዳ ታላቅ ድርሰት ጽፎአል:: የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንም ይህን የሥነ መለኮት መድበል ለዘመናት ጠብቃ ስትጠቀምበት ኖራለች::(21) እንግዲህ በአጭሩ የዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የነገረ ማርያም አስተምህሮ ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ የደረሰበት ወቅት ሊሆን የቻለው ከላይ በገለጥነው ምክንያት ነው::

በቤተ ክርስቲያናችን ታሪክ እንደተጻፈው የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን የነገረ ማርያም አስተምህሮ በስፋትና በጥልቀት የሚገልጹ የተለያዩ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ቅዱሳት ሥዕላት በብዛት መሣልና መታየት የጀመሩትም በዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት ነው:: የኦርቶዶክሳውያን ቅዱሳት ሥዕላትን ምንነት አስመልክቶ ፍራንኮይስ ሺመክ [Francois Schmuck] የተባለው ሊቅ

ጥንታዊትና ታሪካዊ በታ ናት:: Taddese Tamrat (Professor), "Some Notes on the Fifteenth Century Stephanite 'Heresy,' " *RSE* vol. xxii, 103-107.

(21) Getachew Haile (Professor), "The Cause of the Ǝstifanosites: A Fundamentalist Sect in the Church of Ethiopia," *Paideuma* 29 (1983) 93-101. Tadesse Tamrat (Professor), "Some Notes on the Fifteenth Century Stephanite 'Heresy,'" 110 - 115.



ሲናገር «ኦርቶዶክሳዊ ሥነ ሥዕል የክርስቲያናዊ ምሥጢር አጠቃላይ ሥዕላዊ ትርጓሜ ነው»(22) በማለት መስክሮአል:: በኦርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያ ናት ትውፊት መሠረት ለመጀመሪያ ጊዜ ምስለ ፍቁር ወልዳ የተሰኘችውን የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያምን ሥዕል የሳለው ከአራቱ ወንጌላውያን መካከል አንዱ የሆነው ቅዱስ ሉቃስ ወንጌላዊ ነው::(23)

ሐዋርያዊት የሆነችው ቤተ ክርስቲያናችን በአፍም በመጽሐፍም ከምታስተምረው አማናዊ ትምህርቷ ባሻገር ስለ ነገረ ማርያም የምታምነውንና የምታስተምረውን መሠረተ እምነቷን በእነዚህ ቅዱሳት ሥዕላት አማካይነት ትገልጻለች፣ ታስተላልፋለች:: በኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት መንፈሳዊ ትርጓሜ መሠረት ቅዱሳት ሥዕላት የባለ ሥዕሉን ሰማያዊ ጸጋና መንፈሳዊ በረከት ለምእመናን የሚያስተላልፉ ሃይማኖታዊ ንዋያተ ቅድሳት ናቸው:: በዚህም መሠረት ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች ለቅዱሳት ሥዕላት የሚያሳዩት ልዩ ፍቅርና አክብሮት ለባለ ሥዕሉ ያላቸውን ጥልቅ ፍቅርና ፍጹም መንፈሳዊ አክብሮት በግልጥ የሚያሳይና የሚያስረዳ አማናዊ ምስክር ነው::(24)

(22) Francois Schmuck, "Iconography and Ecumenism," *The Eastern Churches Quarterly* Vol. 16, No. 2 (1964), 58.

(23) Leonid Ouspensky, *Theology of the Icon,* trans. Anthony Gythiel (Crestwood, New York: St. Vladimir's Seminary Press, 1992), 60. *መጽሐፈ ስንክሳር ከመስከረም እስከ የካቲት፣* (አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ 1991 ዓ.ም.)፣ ገጽ 46:: Jaroslav, *Mary Through the Centuries: Her Place in the History of Culture,* 18. ከዚህ በተጨማሪ ኢትዮጵያዊ ሥነ ሥዕልን አስመልክቶ ሰፋ ያለና በጥልቅ ጥናትና ምርምር ላይ የተመሠረተ ግንዛቤ ለማግኘት ከዚህ የሚከተለውን መጽሐፍ መመልከት በእጅጉ ይጠቅማል:: Skira, *Ethiopian Icons: Catalogue of the Collection of Ethiopian Studies Addis Ababa University* (Milan: Fondazione Carlo Leone Montandon, 2000), 13-48.

(24) ቅዱስ ሲኖዶስ፣ *የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትናንትናና ዛሬ፣* ገጽ 61-62:: አባ ጎርጎርዮስ፣ *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፣* ገጽ 110-120:: Luigi Gambero, *Mary and the Fathers of the Church: The Blessed Virgin Mary in Patristic Thought* (San Francisco: Ignatius Press, 1999), 388. ሀብተ ማርያም ወርቅነህ (ሊቀ ሥልጣናት)፣ *ጥንታዊ የኢትዮጵያ ሥርዓተ ትምህርት፣* (አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ቀ. ኃ. ሥ. ማተሚያ ቤት፣ 1963 ዓ.ም.)፣ ገጽ 270-274:: Leo Donald Davis, *The Seven Ecumenical Councils (325-787): Their History and Theology* (Wilmington, Delaware: Michael Glazier, Inc., 1987) , 294-295, 310.

ስለሆነም ቅዱሳት ሥዕላት ኦርቶዶክሳውያን ለእመቤታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም ያላቸው ፍጹም ፍቅርና መንፈሳዊ አክብሮት የበለጠ እንዲዳብርና እንዲጸና ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል:: በአገራችን የቅዱሳት ሥዕላት ታሪክ እንደምንረዳው የቤተ ክርስቲያናችን ገዳማት የተጋድሎ ሕይወትና የመንፈሳዊ ትምህርት ማዕከል ከመሆናቸውም በተጨማሪ የሥነ ሥዕላት ጥበብ መሠረት እንደመሆናቸው መጠን አብዛኞዎቹ ሀገር በቀል የሆኑ የቤተ ክርስቲያናችን ሠዓልያን ገዳማውያን አበው ናቸው::[25]

ኢትዮጵያዊው የታሪክ ምሁር ፕሮፌሰር ታደሰ ታምራት እንደገለጹት እስጢፋኖሳውያን ከእናት ቤተ ክርስቲያን ጋር ወደ ነበራቸው አንድነት የተመለሱት በአሥራ አምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ ላይ ነው:: ይህም ሊሆን የቻለው ከእስጢፋኖሳውያን ወገን የሆኑትና ገብረ መሲሕና ዕዝራ የተባሉ ሁለት ልዑካን ባደረጉት ከፍተኛ ጥረት ነው:: በዚህም መሠረት ዕዝራ በንጉሡ በዘርዐ ያዕቆብ ችሎት በተካሄደው ጉባኤ ፊት እስጢፋኖሳውያን ቅድስት ድንግል ማርያምን እንደሚያከብሩ በግልጽ አረጋግጦ ተናግሮአል:: ይህንንም በጉባኤው አዳራሽ ውስጥ በነበረችው ሥዕለ ማርያም ፊት የጸጋ ስግደት በማቅረብ

(25) በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ መሠረት ቅዱሳት ሥዕላት ዘርፈ ብዙ የሆነ ሃይማኖታዊና መንፈሳዊ ዓላማ አላቸው:: ከእነዚህም መጠነ ሰፊ ጠቀሜታዎች መካከል አንዱና ዋነኛው የአማንያንን ሃይማኖታዊ ግንዛቤ ማስፋትና መንፈሳዊ ሕይወታቸውን ማዳበር ነው:: በዚህም ምክንያት በኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች ዘንድ በቅዱሳት ሥዕላት ፊት ሻማ አብርቶና ቆሞ ወይም ተንበርክኮ መጸለይና መማጸን በሰፊው የታወቀና የተለመደ የዕለት ተዕለት መንፈሳዊ ተግባር ነው:: ከዚህም ጋር በዘወትር የቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓተ ጸሎትና ቅዳሴ ጊዜም አበው ካህናት ቅዱሳት ሥዕላትን በመዓዛ ዕጣን ያጥናሉ:: ምክንያቱም ሥዕላቱ የምዑዝ ባሕርይ የእግዚአብሔር ረድኤትና ክብር መገለጫዎች ናቸውና ነው:: በዚህም መሠረት ኦርቶዶክሳውያን ምእመናን በቅዱሳት ሥዕላት አማካይነት እመቤታችንን የሚማጸኑት ከልዑል እግዚአብሔር ዘንድ የተሰጣትን የአማላጅነት ቃል ኪዳን ፍጹም በማመን እንጂ ፈጣሪ ናት ብለው አለመሆኑ ግልጽ ነው:: Heldman, *The Marian Icons of the Painter Fre Seyon: A Study in Fifteenth Century Ethiopian Art, Patronage, and Spirituality*, 19, 80, 91, 96, 113, 163-166. Getachew Haile (Professor), *The Mariology of Emperor Zara Yaqob of Ethiopia*, 4. Thomas Bloosper, *The Virgin Birth* (Philadelphia: The Westminster Press, 1952), 47. ዘርዐ ያዕቆብ፣ «መስተብቁዕ ዘእግዝእትነ ማርያም፣» *መጽሐፈ ቅዳሴ* (አዲስ አበባ፤ አክሱም ማተሚያ ቤት፣ 1993 ዓ.ም.)፣ ገጽ 497::



ከዚያም ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር ለአባታችን ለአዳም የሰጠው የተስፋ ድኅነት ቀጠሮ በደረሰ ጊዜም በመልአከ ሰላም በቅዱስ ገብርኤል ቃለ ብሥራት መሠረት መድኅነ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስን በኅቱም ድንግልና ፀንሳ፣ በኅቱም ድንግልና ወልዳለች:: ወላዲተ አምላክ ልጇ መድኅን ክርስቶስን ድንግልናዊ ወተትን ያስገኙ ጡቶቿን እያጠባች አሳደገችው፤ በክንዶቿ ታቅፋ፣ በጀርባዋ አዝላ ተንከባከበችው:: እመቤታችን በንጉሥ ሄሮድስ ክፋት ምክንያት ወደ ምድረ ግብፅ የተሰደደች፣ በማስተማር ጊዜውም አብራ የተንከራተተች፣ ለቤዛ ዓለም በቀራንዮ አደባባይ በተሰቀለበት ዕለትም ከእግረ መስቀሉ ሥር ያልተለየችና በልጇ ሕማምና ሞት ምክንያት ልቡናዋ ፈጽሞ የተሰበረ የኃዘን እናት ሆነች::

ቤዛዊተ ዓለም ድንግል ማርያም በዕለተ ዓርብ የጌታ ወዳጅ በሆነው በቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ አማካይነት ለዓለም ሁሉ እናት ሆና በጸጋ ተሰጥታለች:: በመሆኑም በቤተ ዮሐንስ ለአሥራ አምስት ዓመታት ያህል ቆየች:: ከዚያም መዝገበ በረከት የሆነችው እመቤታችን ከሥላሴ ዘንድ የምሕረት ቃል ኪዳን ተቀብላለች:: በመጨረሻም የዚህን ኃላፊ ዓለም የእንግድነት ዘመኗን ፈጽማ በስልሳ አራት ዓመቷ በክብር ዐርፋለች::

እመ ሕይወት ድንግል ማርያም ትንሣኤና ፍልሰት፣ እንዲሁም በፍጹም ክብር ማረግና በልጇ በወዳጇ ቀኝ በክብር መቆም የተሰጣት ናት:: በመሆኑም ከላይ በዝርዝር በገለጥነው መሠረት እናትነቷንና ዘለዓለማዊ ድንግልናዋን፣ ንጽሕናዋንና ቅድስናዋን፣ አማላጅነቷንና ክብሯን የምንማርበትና የምናስተምርበት ኦርቶዶክሳዊ መሠረተ እምነት ነገረ ማርያም ይባላል::[29]

(29) *መጽሐፈ ልደታ ["The Book of the Nativity of St. Mary"]*, ed. M. Chaine *Corpus Scriptorum Christianorum Orientalium*, vol. 7 *Scriptores Aethiopici*, t. 22-23 (Text) (Rome: Excudebat Karolus De Luigi, 1909), 3-9, 17-19. *መጽሐፈ ቅዳሴ*፣ (አዲስ አበባ፤ አክሱም ማተሚያ ቤት፣ 1993 ዓ.ም.)፣ ገጽ 168-169:: አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣

በአጠቃላይ የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ነገረ ማርያም አስተምህሮ ስፋትና ጥልቀት፣ ርቀትና ምጥቀት ያለው ነው:: በመሆኑም የምሥጢሩን ልክና መጠን በዚህ አነስተኛ መጽሐፍ ለመወሰንና ለመገደብ የማይቻል በመሆኑ ለነገረ ማርያም ትምህርት መሠረታዊ የሆኑትን አራት ዋና ዋና መሠረታዊ ነጥቦችን እንመለከታለን:: እነዚህም:- ቤዛዊተ ዓለም ድንግል ማርያም በነገረ ድኅነት ውስጥ ያላት ሰፊና ልዩ ድርሻ፤ እመ አምላክ፣ ወላዲተ አምላክ መሆኗ፤ ዐትረ ድንግል ማርያም (ዘለዓለማዊት ድንግል ማርያም) መሆኗ እንዲሁም ክብረ ቅድስት ድንግል ማርያም የሚሉት ናቸው::

መጽሐፈ አርጋኖን፣ (አዲስ አበባ፤ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ 1996 ዓ.ም.)፣ ገጽ 10-16:: ሰአሊ ለነ ቅድስት፣ ገጽ 259:: ተሾመ ዘሪሁን (መልአከ ታቦር)፣ መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 239-245:: Malaty, *St. Mary in the Orthodox Concept*, 25. Mackenzie, "Mary as an Ecumenical Problem," 39. ውዳሴ ማርያም አንድምታ፣ ገጽ 39፣ 73፣ 124፣ 199-200:: አባ ጎርጎርዮስ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፣ ገጽ 155:: ቅዱስ ሲኖዶስ፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት፣ ሥርዓተ አምልኮና የውጭ ግንኙነት፣ ገጽ 51-55:: Walter J. Burghardt, *The Testimony of the Patristic Age Concerning Mary's Death* (Westminster, Maryland: The Newman Press, 1961), 19-24.



ለተሰብሳቢዎቹ አረጋግጠአል:: ይህም በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ የሚሰጠውን የጋራ ስምምነት ለመድረስ አስችሎአል::[26]

የነገረ ማርያም ትምህርት [Mariology] በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትምህርተ ሃይማኖት (ዶግማ) ውስጥ አንዱና ዋነኛው ክፍለ ትምህርት ነው:: በመሆኑም በቤተ ክርስቲያናችን አስተምህሮ መሠረት ነገረ ማርያም የነገረ ድኅነት መሠረትና ምንጭ ነው:: ምክንያቱም በምክረ ከይሲ ተታልሎ ሕገ እግዚአብሔርን በመተላለፉ በኃጢአት ምክንያት ከፈጣሪው ከእግዚአብሔር አንድነት ተለይቶ የነበረው የሰው ልጅ ወደ አምላኩ የቀረበው፣ በዚህም አጥቶት ይኖር የነበረውን የጥንት ተፈጥሮአዊ ጸጋና ክብር ዳግመኛ በሐዲስ ተፈጥሮ ያገኘው አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም በተዋሕዶ በነሣው ሥጋና ነፍስ መሠረትነት በተፈጸመው አምላካዊ የምሥጢረ ሥጋዌ አድኅኖት ነው::[27] ይህንን

[26] Tadesse Tamrat (Professor), "Some Notes on the Fifteenth Century Stephanite 'Heresy,'" 112-115. በቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደተገለጸው በሉተራውያን የተሐድሶ ንቅናቄ ጊዜም ሆነ ከዚያም በኋላ የተነሡ አንዳንዶች ካለማስተዋል የተነሣ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለእመቤታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም የምትሰጠውን አክብሮት እንደ አምልኮት በመቁጠር ከቤተ ክርስቲያኒቱ አስተምህሮ ውጭ የሆነ የስንፍና ንግግርን ሲናገሩ ይስተዋላሉ:: ከዚህም ሌላ ቤተ ክርስቲያናችን ወላዲተ አምላክ በነገረ ድኅነት ውስጥ ስላላት ሱታፌ የምታስተምረውን መጽሐፋዊ ትምህርት የክርስቶስ የቤዛነት ሥራ ምትክ እንደሆነ አድርገው ይቆጥሩታል:: Timothy Ware, *The Orthodox Church*, New Edition. (London: Penguin Books, 1997), 98-99.

ከላይ ከገለጥነው በተጨማሪም አሜሪካ ውስጥ በሚገኘው ታላቁ የፕሪንስተን ከፍተኛ የሥነ መለኮት ተቋም ውስጥ የአዲስ ኪዳን መምህርት የሆኑት ፕሮፌሰር ቤቨርሊይ ጋቬንታ [Professor Beverely R. Gaventa] በአንድ ወቅት ታይምስ በተሰኘው መጽሔት ላይ ባቀረቡት ጥናታዊ ጽሑፍ አብዛኛውን ጊዜ የፕሮቴስታንት እምነት [Protestantism] በሥነ መለኮት ትምህርቱም ሆነ በሥርዓተ አምልኮቱ ውስጥ የእመቤታችንን ክብርና በነገረ ድኅነት ውስጥ ያላትን አስፈላጊነት አያወሳም በማለት በጥናትና ምርምር አስደግፈው ገልጸዋል:: David Van Beima, "Hail Mary," *Times*, 21 March 2005, 49-50. Anthony J. Tambasco, *What are they Saying about Mary?* (New York: Paulist Press, 1984), 55, See also J. A. Ross Mackenzie, "Mary as an Ecumenical Problem," Alberic Stacpoole, ed., *Mary's Place in Christian Dialogue* (Wilton, Connecticut: Morehouse-Barlow Co., Inc., 1983), 35-37.

[27] መዝሙረ ድንግል፣ (አዲስ አበባ፤ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ 1959 ዓ.ም.)፤ ገጽ 44-46:: ቅዱስ ያሬድ፣ "አንቀጸ ብርሃን"፣ መዝሙረ ዳዊት ወመዝሙር ጸሎት፣ (አሥመራ፤

አስመልክቶ ሶርያዊው ሊቅ ቅዱስ ኤፍሬም ሲናገር «በመንክር ምሥጢር ወለድኪዮ ለአማኑኤል ወበእንተዝ ዐቀበኪ እንበለ ሙስና፤ ድንግል ሆይ ድንቅ በሚያሰኝ የተዋሕዶ ምሥጢር አምላካችንን አማኑኤልን ወለድሽው፤ እርሱም ያለመለወጥ በድንግልና አጸናሽ»(28) በማለት መስክሮአል።

ዳግመኛም ወንጌላዊው ቅዱስ ማቴዎስ አማኑኤል የሚለውን ትንቢታዊ ስያሜ ትርጉም ሲያስረዳ፡- «እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው» (ማቴ. 1÷23) በማለት መስክሮአል። በዚህም አምላክ ሰው፣ ሰው አምላክ የሆነባትና በተዋሕዶ የከበረባት፣ ሰማይና ምድርን ማለትም ሰውና እግዚአብሔርን ያስታረቀ፣ ሰውና መላእክትን እንዲሁም ሕዝብና አሕዛብን ያገናኘና አንድ ያደረገ መድኅነ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ የተገኘ ባትና በሥጋ የተገለጠባት አማናዊቷ ምክንያተ ድኅነት፣ መሠረተ ሕይወት የሆነችው እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም መሆኗን ልብ ይሏል።

ወደፊት በስፋት እንደምናየው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን መሠረተ እምነት የነገረ ማርያም ትምህርት ነገ ረ ሃይማኖት ነው። በመሆኑም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ቅድመ ዓለም በኅሊና አምላክ ታስባ መኖሯን፣ የድኅነተ በዓለም ተስፋ በተሰበከበት በዘመነ አበው በተለያየ ኅብረ አምሳል መገለጧን፣ ኋላ በዘመነ ነቢያት ደግሞ በተለያየ ኅብረ ትንቢት መነገሯን እንማርበታ ለን። ቤዛዊተ ዓለም ድንግል ማርያም በፈቃደ እግዚአብሔር ከቅዱስ ኢያቄምና ከቅድስት ሐና ተወልዳ የብፅዓት ልጅ እንደመሆኗ መጠን በሦስት ዓመቷ አማናዊት ቤተ መቅደስ ድንግል ወደ ቤተ መቅደስ ገብታ አሥራ ሁለት ዓመት በንጽሕና በቅድስና ኖራለች።

ኮከበ ጽባሕ ማተሚያ ቤት፣ 1983 ዓ.ም.)፣ ገጽ 402። ዓምደ ወርቅ እስጢፋኖስ (መሪ ጌታ)፣ «እመቤታችን በቅዱስ ያሬድ ጸዋትወ ዜማ፣» *ሐመር ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ፣* ሚያዝያ/ግንቦት 30/1991 ዓ.ም. ገጽ 8። *መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣* (አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1988 ዓ.ም)፣ ገጽ 228-229።

(28) *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣* ገጽ 176።



## የክለሳ ጥያቄዎች

1. በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተ ምህሮ መሠረት ነገረ ማርያም ማለት ምን ማለት ነው?
2. ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የነገረ ማርያም ትምህርት ዕ ድገትና መስፋፋት ዋና ዋና ምክንያቶቹ ምን ምንድን ናቸው?
3. የክርስትና ሃይማኖት ወደ አገራችን ወደ ኢትዮጵያ መቼ፣ በማንና እንዴት እንደገባ በአጭሩ ያብራሩ።
4. የእስክንድርያው ሊቅ አርጌንስና ታዋቂው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊ አውሳብዮስ ስለ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ምን ተናገሩ? ምንስ መሰከሩ?
5. በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተከናወኑት ዋና ዋና ዐበይት ተግባራት ምን ምንድን ናቸው?
6. ስለ ተሰዓቱ (ዘጠኙ) ቅዱሳን ያለዎትን ግንዛቤ በአጭሩ ይግለጹ።
7. ስለ ኦርቶዶክሳውያን ቅዱሳት ሥዕላት ምንነትና መንፈሳዊ ጠቀሜታ ምን ያህል ተገንዝበዋል?
8. በአሥራ አምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአገራችን የነበ ረው የታላቁ ንጉሥ የዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት የቤተ ክርስቲያናችን የነገረ ማርያም አስተምህሮ ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ የደረሰበት ወቅት ነው መባሉ ስለምንድን ነው?

በመምህር አንዱዓለም ዳግማዊ /B.Th. M.A/
ሚያዝያ/1998 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

andudag@yahoo.com
andudag.dagmawi@utoronto.ca